# ETHIOPIAN PUBLIC SERVICE UNIVERSITY

# የኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

Quarterly Manazine
June - Sept 2025




## በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲካሄድ የነበረው የኢሲሰዩ የወደፊት አቅጣጫ ይፋ ሆነ

## የኢፐሰዩ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የቁልፍ ተግባራት አፈጻጸም የፊርማ ስነሥርዓት አካሄደ







## በኢሲሰዩ የአዲስ ምዕራፍና የለውጥ ጉዞ ሂደትን አስመልክቶ ለተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጠ።

## ECSU President and GIZ Explore Collaborative Opportunities



## Our Mission

The University exists to deliver specialized and high-quality education, research, training, consultancy and community engagement programs thereby contributing towards the development of competent and innovative public sector through public entrepreneurship.

## Our core values

- Moral Integrity:
- Excellence and Professionalism:
- Accountability and Transparency
- Problem Solving:
- Diversity and Inclusiveness:

# Table of contents


በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲካሄድ የነበረው የኢሲሰዩ የወደፊት አቅጣጫ ይፋ ሆነ........................................................1

በኢሲሰዩ የአዲስ ምዕራፍና የለውጥ ጉዞ ሂደትን አስመልክቶ ለተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጠ።........................................................................................................................3

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም የጥናት ውጤት እና የለውጥ ጉዞ ማስፈጸሚያ ዕቅድ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ ግብር ተካሄደ....................................................................................4

የኢሲሰዩ ለጀመረው የሪፎርም ትግበራ ረቂቅ ሰነድ ለማዘጋጀት ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች ገለጻ ተሰጠ..................6

የሪፎርም ስራ ኮሚቴ አባላት የስራዎቻቸዉን ሂደት ገመገሙ..................................................................7

የኢፐሰዩ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የቁልፍ ተግባራት አፈጻጸም የፊርማ ስነሥርዓት አካሄደ..........................8

የኢሲሰዩ ለሁለት አረጋውን የቤት እድሳት ድጋፍ ለማድረግ ግንባታ አስጀመረ.............................................9

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች የችግኝ ተከላ አካሄዱ...........................................................9

18ኛው ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን በኢሲሰዩ ተከበረ...................................................................10

በኢሲሰዩ የማዕድ ማጋራት መርሀ-ግብር ተከናወነ.........................................................................10

ECSU President and GIZ Explore Collaborative Opportunities.....................................................11

Case Teaching Workshop Held at ECSU........................................................................................12

# በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲካሄድ የነበረው የኢሲሰዩ የወደፊት አቅጣጫ ይፋ ሆነ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (ኢሲሰዩ) የወደፊት አቅጣጫ ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲካሄድ የቆየው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም ጥናት ውጤት የኢሲሰዩ የወደፊት የአዲስ ምዕራፍ የለውጥ ጉዞ ማብሰሪያ በሚል በተዘጋጀው መርሀ-ግብር የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትርና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር በተገኙበት መስከረም 5 ቀን 2018 ዓ.ም ይፋ ተደረገ፡፡




በሪፎርም ጥናት ውጤት ማብሰሪያ መድረኩ ላይ የተገኙት የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ በሰጡት አቅጣጫ ዩኒቨርሲቲው ኢትዮጵያን ወደፊት የሚያራምዱ፣ ብቃትን የተላበሱ እና ነጻና ገለልተኛ በመሆን፤ በጥሩ በሥነ ምግባር የታነጹ፣ በአጠቃላይ ለሁኔታዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የሚችሉ፣ ሲቪል ሰርቫንት ማፍራት ተቀዳሚው አላማው መሆኑን ገልጸው ዩኒቨርሲቲው ከዚህ በኋላ እስካሁን በመጣበት አካሄድ መቀጠል የማይችል በመሆኑ፣ እራሱን በመለወጥ ወቅቱ ከሚጠይቀውና ሀገራዊ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርሙን በተገቢው ሁኔታ ማገዝ የሚችል እንዲሆን፤ ይህን ተልዕኮም ለመወጣት አዲስ አቅጣጫን መከተል እንደሚገባ በአጽንኦት ተናግረዋል፡፡ የቀረበው ጥናትም ቀደም ሲል የነበረውን የዩኒቨርሲቲውንና የኮሚሽኑን የተጣረሰ ግንኙነት የሚያስተካከል መሆኑን የገለጹት ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ ጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ የሌለው ሀገር ጠንካራ ሀገር እንደማይሆን በመግለጽ ዩኒቨርሲቲውም እራሱን በመሰረተ- ልማትና በአካዳሚክ ዘርፉም አጎልብቶና አሳድጎ ሀገራዊ ሪፎረሙን መተግበር የሚችል ፣ ሙያውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሲቪል ሰርቫንት በማፍራት ላይ ጠንክሮ መስራት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር መኩሪያ ኃይሌ በበኩላቸው ኮሚሽኑ ሀገራዊ ሪፎርሙን መሰረት በማድረግ ነጻ፣ መንግስት ተሻጋሪ፣ ገለልተኛና ብቁ ሲቪል ሰርቫንትን ለመፍጠር እየሰራ መሆኑን አመልክተው፣ ይህን ተልዕኮ መሸከም የሚችል ሲቪል ሰርቫንት በሚፈለገው ደረጃ አለመኖሩ በሂደቱ ላይ ተግዳሮት እየፈጠረ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሆነውም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የተሸከመው ተልዕኮም እጅግ ከፍተኛ መሆኑን በማመላከት እራሱንም ወደሚፈለገው ስታንደርድ በማሳደግ ልዕቀትን፣ ምሉዕ ሰብዕናን እንዲሁም ፈጠራንና ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት እንዳለበት ብሎም ወደ አለም አቀፍ ደረጃ መምጣት እንደሚገባው ዶ/ር መኩርያ ኃይሌ አሳስበዋል፡፡ የኢሰዩ ፕሬዚደንት ዶ/ ንጉስ ታደሰ ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የዕለቱ መርሀ-ግብር ተቀዳሚ



ዓላማ በዋናነት በሚቀርበው የጥናት ውጤት ላይ ግብዓት የሚሆን የሀሳብ እና በወደፊት የትግበራ ሂደት ላይም የጥናቱን ውጤት በአግባቡ ለመተግበር እንዲቻል ግንዛቤን መፍጠር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ጥናቱም በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ሲቪል ሰርቪስ ለማዘመን የተጀመረውን ሪፎርም ለማገዝ እና ዩኒቨርሲቲዎችን በሀገር ደረጃ ያሉበትን ስታንደርድ የመለየት ሂደትን እንደ መነሻ ሀሳብ አድርጎ የተደረገ ጥናት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ጥናቱም በከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም የአካደሚክ ባለሙያዎች እየታገዘ በመሰራቱ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ከተደረገው ጥናት የተሻለ እንደሚያደርገው ተናግረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም የጥናት ውጤትም ዩኒቨርሲቲው የወደፊት አቅጣጫ ምን መምሰል እንዳለበትና የሚመራበትም የህግ ማዕቀፍ የሚያሳይ ዝርዝር ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ በጥናቱ ውጤት እንደተመላከተውም የዩኒቨርሲቲው Public Service and University በሚል ስያሜ እና ቀደም ሲል እንደነበረው ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ በመሆን የሚቀጥል ሲሆን ፤





በመሰረታዊነት ሀገራዊ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ሪፎርሙን የሚያግዝ ጠንካራ ሲቪል ሰርቫንት የማፍራት ፣ የትኩረት አቅጫውን በፐብሊክ ሰርቪስ ላይ ያደረገ፣ በማህበራዊ ሳይንስ እና ዲቨሎፕመንት ስተዲስ፣ ፐብሊክ ሴክተር ቢዚንስ እና ምጣኔ ሀብት እንዲሁም በዲጂታላይዜሽን እና በፐብሊክ ሰርቪስ ኢኖቬሽን በትኩረት የሚሰራ መሆኑን እና የዩኒቨርሲቲው የወደፊት አቅጣጫ ምን መምሰል እንዳለበትና የሚመራበትም የህግ ማዕቀፍ ላይም የአካዳሚክ መዋቅር እና የትምህርት መርሀ-ግብር ቀረጻ፣ የተማሪዎች እና የስታፍ መረጣ፣ የምርምር ፣ የስልጠና እና የማማከር የማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አካቶ ቀርቧል፡፡ በጥናቱ ውጤት ላይም ከተሳታፊዎች የተለያዩ ሀሳብና አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን ከመድረክም ለተነሱት ሀሳብና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥተዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትን በአግባቡ ለመተግበር እና ዩኒቨርሲቲውን ወደአዲስ ምዕራፍ ለማሻገር በሚደረገው ጥረትም የኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴርና የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንም በሙሉ ኃይል ለማገዝ ያላቸውን ቁርጠኝነትም ገልጸዋል፡፡





# በኢሲሰዩ የአዲስ ምዕራፍና የለውጥ ጉዞ ሂደትን አስመልክቶ ለተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጠ፡፡

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (ኢሲሰዩ) የወደፊት አቅጣጫ ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲካሄድ የቆየው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም ጥናት ውጤት እና የዩኒቨርሲቲው የወደፊት አዲስ የለውጥ ጉዞ ሂደትን አስመልክቶ ለተለያዩ የሚዲያ አካላት የኢሲሰዩ ፕሬዚደንት ዶ/ር ንጉሥ ታደሰ መስከረም 22 ቀን 2018 ዓ.ም በሴኔት አዳራሽ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫውም ዩኒቨርሲቲው ላለፉት ሶስት አሰርት




ዓመታት የሀገሪቱን የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት በትምህርትና በስልጠና አቅማቸውን ሲገነባ የቆየ መሆኑን አስታውሰው በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሁለተኛውን ምዕራፍ የለውጥ ጉዞ መጀመሩን ገልጸዋል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ጉዞውም ዩኒቨርሲቲው ምን መምሰል እንደሚገባው እና በምን መልክ ሊደራጅ እንደሚገባው የሚያጠና ሀገራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ ለዘጠኝ ወራት ባደረገው ጥናት ዩኒቨርሲቲው በአዲስ መልክ ለመደራጀት በሚያስችሉት የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮ፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ የሚመራበት ፍልስፍና እና እሴቶችን የመለየት ሥራዎች መሰራታቸውን ገልጸው በጥናቱ ውጤት መሰረትም ዩኒቨርሲቲው በተግባራዊ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ምድብ ስር የተካተተ መሆኑን በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ተናግረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ተልዕኮም ብቃትና ጥሩ ሥነ-ምግባር ያለው ምሩቃንን ማፍራት እና የፐብሊክ ሴክተሩን በፈጠራ፣ ዲጂታላይዜሽን እና በስልጠና የተቋማትን አቅም መገንባት መሆኑን ገልጸው የትኩረት አቅጣጫውም በአመራርና አስተዳደር፣ በፐብሊክ ሰርቪስ ሪፎርም፣በማህበራዊ ሳይንስና ማህበራዊ ልማት ፣ በፋይናንስና ኢኮኖሚክስ፣ በህግና በዲጂታላይዜሽንና ፈጠራ ላይ አተኩሮ እንደሚሰራ በጋዜጣዊ መግለጫቸው አመላክተዋል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረትም የአካዳሚክ ፕሮግራሞች የተለዩ መሆናቸውን ጠቅሰው የፐብሊክ ሴክተር የሪፎርም ሥራዎችን የሚያግዝ ማዕከል እና ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የስልጠና ማዕከል ለማቋቋም እንዲሁም አጠቃላይ የሪፎርሙ ጉዞ ማስፈጸሚያ ዕቅድ በስፋት እየተሰሩ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ተቋማትን በፈጠራና በኢኖቬሽን የማገዝ፣ የተማሪዎች ምንጨም ከሲቪል ሰርቪስ ተቋማትና ከአስራ ሁለተኛ ክፍል ተፈታኞች በቀጥታ መቀበል መቻሉ እንዲሁም በትምህርት ፕሮግራሞች አደረጃጀት ማለትም በጋራ ኮርሶች፣ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የማይሰጥ ነገር ግን በዚህ ዩኒቨርሲቲ ብቻ የሚሰጥ ፋውንዴሽናል ኮርሶች መኖሩ እና በሙያዊ ኮርሶች መደራጀቱ ዩኒቨርሲቲውን ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ልዩእንደሚያደርገው ተናግረዋል፡፡ በርካታ የሪፎርም ሥራዎች



በስፋትእየተሰሩመሆናቸውንናበአሁኑወቅትምየዩኒቨርሲቲው በትምህርት ሚኒስቴር የተማሪዎች ምርጫ መካተቱን ጠቅሰው የዩኒቨርሲቲው የመጨረሻ መዳረሻም ራስ -ገዝ ዩኒቨርሲቲ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም ከጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

# በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም የጥናት ውጤት እና የለውጥ ጉዞ ማስፈጸሚያ ዕቅድ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ ግብር ተካሄደ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (ኢሲሰዩ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲካሄድ የቆየው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም ጥናት አጠቃላይ ውጤት ይፋ መደረጉን ተከትሎ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ ግብር ተካሄደ ። መስከረም 21 ቀን 2018 ዓ.ም በአባይ አዳራሽ በተካሄደው የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ-ግብር ላይም ሁሉም የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ እና የአስተዳደር ሰራተኞች ተሳትፈዋል።




በመርሀ-ግብሩ መክፍቻ ላይም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ዶ/ር ንጉሥ ታደሰ መርሀ ግብሩ ለአካዳሚክና ለአስተዳደር ሰራተኞች በተናጠል ሲቀርብ የቆየውን የጥናት ውጤት ላይ በጋራ በመነጋገር እንደ አንድ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የጋራ በማድረግ በተቋም ደረጃ ተመሳሳይ አቋምና አረዳድ እንዲኖር ማስቻል ብሎም ከለውጥ ዝግጅት ምዕራፍ ወደትግበራ ሂደት መገባቱ የሚታወጅበት መርሀ-ግብር መሆኑን ገልጸዋል። አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው ወደ ሪፎርም ዕቅድ ትግበራ ሲገባ በዩኒቨርሲቲው ያሉትን መልካም ዕድሎችና ተግዳሮቶች በመለየት ዕቅዱን እንዴት መተግበር እንደሚገባው በጥልቀት ማሰብ ተገቢ መሆኑን ጠቁመው ለዕቅድ መዳበርም ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አስተዋጽኦ የሚያደርግበት መድረክ መሆኑን በመገንዘብ በንቃት መሳተፍ እንደሚገባው አሳስበዋል።

በማሳከተልም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም



ጥናት ውጤት በዶ/ር አማኑኤል ኩሲያ የቀረበ ሲሆን ቀደም ሲል በጥናቱ ውጤት ላይ ሲነሱ የቆዩ እና የጋራ ግንዛቤን በሚሹ ጉዳዮች ተለይተው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። በቀረበው የጥናት ውጤትና ማብራሪያ ላይም ከቤቱ በተነሱ አሰተያየቶችና ጥያቄዎችም ማብራሪያና ምላሽ ተሰጥቷል። ከጥናቱ ውጤት ውይይት በማስከተልም የዩኒቨርሲቲው የለውጥ ጉዞ ማስፈጸሚያ ዕቅድ በዶ/ር ንጉሥ ታደሰ የቀረበ ሲሆን በዕቅዱም አጠቃላይ የሁኔታዎች ትንተና እና የዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች መዳረሻ በዝርዝር ቀርቧል። በዩኒቨርሲቲው ያለው የሰው ኃይል ስብጥርና ብቃት፣ የሚገኝበት ስትራቴጂያዊ ቦታና ፣ ጠንካራ መሰረተ-ልማቶች መኖር እንዲሁም ለተቋሙ በመንግስት የተሰጠው ትኩረት እንደ ጥናካሬና መልካም አጋጣሚዎች በመጥቀስ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችንም ዘርዝረዋል።አያይዘውም የዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂካዊ ጉዳዮችም :- በተቋሙ የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች ጥራት ፣ ተገቢነትና አለምአቀፋዊ ዕውቅና ያላቸው ማድረግ፣ ተቋሙን የዩኒቨርሲቲ ባህሪ ማላበስ፣ ብቃትና ስነ-ምግባር የተላበሱ ተመራቂዎችን ማፍራት፤ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የሙያ ስልጠና ማዕከል ማደራጀትና ጥራታቸውን የጠበቁ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠናዎችን መስጠት ፤ በሀገራዊ ሪፎርም መንግስታዊ ተቋማትን ማገዝ እና ማዘመን፣ ተግባራዊ ምርምር እና የፖሊሲ ተጽእኖ ላይ ትኩረት ማድረግ፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ምሁራንን ማፍራት፣ ዓለም አቀፋዊነትን ማሳደግ እንዲሁም የአስተዳደርና የፋይናንስ ራስ-ገዝነትን መገንባት የዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂያዊ መዳረሻዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይ የሚከናወኑ ስራዎችና ግቦችን በተመለከተም ከ2019-2023 የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮና የትኩረት መስክ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮና የትኩረት መስክ ማስፈጸሚያመዋቅር ማዘጋጀት፣ በፐብሊክ ሴክተሩ ተፈላጊ የሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች ማዘጋጀት እንዲሁም አለማቀፍና ሀገር አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ ማልማት፣ ተማሪዎችን በሥነ-ምግባር ፣በአቅምና ችሎታ ማብቃት፣ ነባርና ዋና ዋና የአካዳሚክ ህጎችን በመከለስ ከተሻሻለው ተልዕኮ ጋር ማጣጣም ፣ የፐብሊክ ሴክተሩን ችግር የሚፈቱ ምርምሮችንና ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀት፣ የፐብሊክ ሴክተር ፈጠራና አስተዳደር ማዕከል ማደራጀት፣ ደረጃውን የጠበቀ ፋሲሊቲዎችን መገንባት፣ የአስተዳደር አሰራሮችን በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ማዘመን፣ ነጻ ገለልተኛና ከመንግስት የበጀት ጥገኝነት ነጻ የወጣ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መገንባት፣ የዩኒቨርሲቲውን ስም ማደስና ዓለምአቀፋዊነትን ማሳደግ እንዲሁም ተቀባይነት ያላቸውና ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ምሁራንን እና ተመራማሪዎችን ማፍራት ዩኒቨርሲቲው በትኩረት እየሰራባቸው ያሉ እና አንዳንዶቹም በመጠናቀቅ ላይ ያሉ ግቦች መሆናቸውን ዶ/ር ንጉሥ ገልጸዋል።

በቀረበው ሪፖርትና እቅድ ላይም ከተሳታፊዎች የተለያዩ ሀሳብና አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን ለተነሱት ሀሳብና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥተዋል።





# የኢሲሰዩ ለጀመረው የሪፎርም ትግበራ ረቂቅ ሰነድ ለማዘጋጀት ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች ገለጻ ተሰጠ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ዛሬ ነሐሴ 26 ቀን 2017 ዓ/ም በህዳሴ አዳራሽ ባካሄደው ስብሰባ ወደ አዲስ ምዕራፍ በሚያደርገዉ ሽግግር ለሁለተኛው ዙር የሪፎርም ትግበራ የሚረዱ ሰነዶችን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በተዋቀሩት ኮሚቴዎች ውስጥ ለሚሳተፉ የአካዳሚክ እና የአስተዳደር ሰራተኞች ገለጻ ተሰጠ።



በመረሀ-ግብሩ መክፈቻ ላይ የኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሥ ታደሰ እንዳስቀመጡት ዩንቨርስቲዉ በለዉጥ ሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዉ ፣የለዉጥ ስራዎቹም በተለያዩ ምዕራፎች የሚከናወኑ መሆናቸውንና የአጭርና የረጅም ጊዜ መዳረሻዎችን በጥልቀት የሚያመላክቱ ተግባራት ተለይተዉና አቅጣጫ ተቀምጦባቸዉ የሚተገበሩ ይሆናል ብለዋ። በቅርቡም አጠቃላይ የሪፎርም ሂደቱ በተመለከተ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋመዉ አብይ ኮሚቴ የጥናት ዉጤቱን ይፋ እንደሚያደረግ ገልጸዋል።ነገር ግን በትይዩ ስራዎቻችን ማከናወን ስላለብን የተለያዩ የዉስጥ የኮሚቴ አደረጃጀቶች የተዋቀሩ ሲሆን ፤የተደራጁት የለዉጥ ስራዎች አስተግባሪ ኮሚቴዎች የመጀመሪያ ዙር የለዉጥ ስራዎች አስተግባሪ ኮሚቴ በ ዘጠኝ ኮሚቴዎች የተደራጀ መሆኑን በመግለጽ ዝርዝር ስራዎቻቸዉን ለኮሚቴዉ አስተዋውቀዋል። እነዚህ ኮሚቴዎቹ በዋናነት በአጭር ግዜ የሚተገበሩ ግዜ የማይሰጡ ተግባራት ላይ በማተኮር እየሰሩ መሆኑንን ገልጸዋል።በዛሬዉ ዕለት ይፋ የሆነዉ የሁለተኛ



ዙር ወደ ስራ የሚገቡ የለዉጥ ስራዎች የሚያከናዉኑ 26 ኮሚቴዎች የተደራጀ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህም ተግባር የዩኒቨርስቲዉ ማህበረስብ ተቋሙን በመለወጥ ሂደት ዉስጥ የራሱን አሻራ ማስቀመጥ አለበት ብለዋል። የተደራጁት ኮሚቴዎችም ልዩ ድጋፍ እና ክትትል በማናጅመንቱ የሚደረግላቸዉ መሆኑን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ ኮሚቴዎች የሚያዘጋጁት ሰነዶችም ለረጅም ግዜ ለተቋም መዳረሻ መሰረት የሚጥሉ፣ጥራታቸዉን የጠበቁ ፣ በወቅቱ የሚጠናቀቁ እና ተተግባሪ መሆን እንዳለባቸዉ በመጥቀስ፤ ይህ ስራ ሲሰራ በእኔነት መንፈስ የጋራ ቤታችንን የምንገነባበት፣ ስማችንን በአዲስ መልክ የምናድስበት መሆን አለበት ብለዋል።

በለዉጥ ስራዎቻችን ላይ ሁሉም የዩኒቨርስቲዉ ማህበረሰብ አንድ አይነት አቅጣጫ ይዘን በእኔነት ስሜት መዳዝ አለብን ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ በየትኛዉም ሂደት የጋራ ራዕይ ይዘን ፣በተግባር የሚታይ ፣መሰረት የሚጥል እና ተሻጋሪ ተቋም መፍጠር የሁላችንም ድርሻ መሆኑን አዉቀን በትኩረት መስራት ግድ ይላል ብለዋል። በመቀጠልም ፕሬዘዳንቱ፣ የኮሚቴዎቹን ተግባርና ኃላፊነት ለመዘርዘር በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ሰፊ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን፣ የሰነዱ ይዘት እያንዳንዱ ኮሚቴ ስራውን ጀምሮ የሚያጠናቅቅበትን ጊዜ፣ የግንኙነት ጊዜ እና ተጠሪነትን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ መሆኑን ገልጸዋል። እያንዳንዱ ኮሚቴ ስራውን አጠናቆ ለመጨረስ እንደስራው ስፋት እና ጥልቀት የተወሰነ የጊዜ ገደብ የተቀመጠለት መሆኑ በሰነዱ ላይ ተመላክቷል። በመጨረሻም ከተሰብሳቢዎቹ ለቀረቡ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ምላሽ ከተሰጠ በኋላ፣ ሁሉም የኮሚቴው አባላት ትኩረት ሰጥተው ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ ስብሰባው አብቅቷል።



# የሪፎርም ስራ ኮሚቴ አባላት የስራዎቻቸዉን ሂደት ገመገሙ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሪፎርም ስራዎች የሚያስተባብሩ የተለያዩ ኮሚቴዎች የስራዎቻቸዉ ሂደት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ የግምገማ መድረክ መስከረም 15 ቀን 2018ዓ.ም አካሄዱ ።



በዚህ ግምገማ መድረክ መክፈቻ ላይ የዩንቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሥ ታደሰ እንደተናገሩት የኢሲሰዩ የወደፊት አቅጣጫ ሀገራዊ የጥናት ቡድን ተቋቁሞ የጥናት ዉጤት መቅረቡን እና የዩንቨርስቲዉ የአዲስ ምዕራፍ ጉዞ ለዩንቨርስቲዉ ማህበረሰብ እና ለአጋር አካላት መበሰሩን፣ በተጨማሪም ቀጣይ አቅጣጫዎችም መመላከታቸዉን ገልጸዋል።የዩንቨርስቲዉም አመራርም ቀድም ብሎ ከጥናቱ ጎን ለጎን የተለያዩ ኮሚቴዎች አደራጅቶ ተቋሙ ወደስራ እንዲገባ የሚያስችል ስራዎችን እየሰራ እንደነበር ገልጸዋል። የዚህ መድረክ አስፈላጊነት ፕሬዚዳንቱ ሲናገሩ ሪፎርሙን ለማስተግበር የተደራጁ ኮሚቴዎች ስራዎቻቸዉ ምን ላይ እንደደረሰ፣የገጠመ ችግር፣በተጨማሪም ስራዎቹ ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ በተቀመጠዉ የግዜ ገደብ በዕቅዳቸዉ መሰረት መሄዳቸዉን የኮሚቲ አባላት በሙሉ በተገኙበት መገምገም አስፈላጊ ስለሆነ ነዉ ብለዋል።

በማስከተልም የየኮሚቴ ሰብሳቢዎች እና አባላት እስካአሁን በኮሚቴዎች የተሰሩ ፣ወደፊት የሚሰሩ እና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች በዝርዝር አቅርበዋል።

በማጠቃለያዉ ላይም የዩንቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት እንደተናገሩት ተቋሙን ለማስቀጠል የነበረበትን ደረጃ ሁሉም አካላት በመረደታቸዉ ወደሪፎርም አስገብተን ስራዎቻችን በዛዉ ልክ በመስራታችን የመጀመሪያዉ የተቋሙ የሪፎርም ጉዞ ጅማሮ ዉጤታማ ነዉ ብላዋል። በተጨማሪም አጠቃላይ የዩንቨርስቲዉ የሪፎርም ስራዎች በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን እና ከዝግጅት ምዕራፍ ወደ ትግበራ ምራፍ በታቀደዉ መሰረተ እየተሸጋገረ እንዳለ ገልጸዋል።

ተቋሙን ሙሉ ለሙሉ መንግስት ባስቀመጠዉ አቅጣጫ ህይወት ዘርቶ እንዲሄድ የሁሉም የዩንቨርስቲዉ ማህበረስብ ከተለመደዉ የስራ ባህሪ በመዉጣት በልዩ ሁኔታ መስራት ግድ ይላል ያሉት ፕሬዚዳንቱ ለዚህም አመራሩ ቁርጠኛ እንደሆነ የሚያስፈልገዉን ነገር በሙሉ እንደሚያቀርብ ገልጸዋል።በማስከተልም በተነሱ ሀሳቦች እና ጥያቄዎች ዙርያ ማብራርያ እና ገለጻ በመስጠት ወደፊት የሚሰሩ ስራዎች ላይ አቅጣጫ በማስቀመጥ ፕሮግራሙ ተጠናቋል።





# የኢፐሰዩ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የቁልፍ ተግባራት አፈጻጸም የፊርማ ስነሥርዓት አካሄደ

የኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሥ ታደሰ እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ በትምህርት ሚኒስቴር በተዘጋጀዉ በቁልፍ ተግባራት የአፈጻጸም አመላካቾች / Key Performance Indicators/ ስምምነት መስከረም 30 ቀን 2018ዓ.ም ተፈራረሙ።




ስምምነቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ 47 የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የቦርድ ሰብሳቢዎች እና የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶች በተገኙበት የተከናወነ ሲሆን ስምምነቱም በዋናነት በትምህርት ዘርፉ በተከናወኑ የሪፎርም ስራዎች መጠነ ሰፊ ለውጥ መመዝገቡን እና የዚህን ቀጣይነት ማረጋገጥ ፣በተለይ ዲጂታላይዜሽንን በማስፋፋት ረገድ በርካታ ተግባራት መከናወን እንደለበት ያመላከተ ሲሆን በቀጣይም የትምህርትን ጥራት፣ ተደራሽነትና አካታችነትን በማሳደግ የትምህር ስርአት ማዘመን የሁሉም ድርሻ እንደሆነ ተመላክቷል።የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራሮችም ይህን ስምምነት በልዩ ሁኔታ ትኩረት በመስጠት በቁርጠኝነት ለአፈጻጸሙ ድርሻቸዉን እንዲወጡ ጥሪ ተላልፏል።



## የኢሲሰዩ ለሁለት አረጋውን የቤት እድሳት ድጋፍ ለማድረግ ግንባታ አስጀመረ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (የኢሲሰዩ) ሰኔ 10 ቀን 2017 ዓ/ም ባደረገው የማህበረሰብ ድጋፍ እንቅስቃሴ፣ ከቆይታ ብዛት የመኖሪያ ቤታቸው ለፈረሰባቸው፣ በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 በተለምዶ አልታድ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ለሚኖሩ ሁለት አቅመ ደካማ እናቶች ቤታቸውን አፍርሶ እንደገና ለመስራት የግንባታ ስራ አስጀመረ።



በማስጀመሪያ ኘሮግራሙ ላይ የተገኙት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ንጉሥ ታደሰ(ዶ/ር) እንዳሉት፣ እንደዚህ አይነቱ ሰው ተኮር የድጋፍ ስራ የመንግስት አቅጣጫ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ሰው በመሆናችን ብቻ ልናከናውነው የሚገባ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል፤ አያይዘውም "በተለይ



እንደእናቶቻችን ያሉ በእድሜ የገፉ ሰዎችን መደገፍ በኃይማኖቶቻችንም ቢሆን ዋጋ የሚያሰጠን ነው።" ብለዋል። ይህ በጎ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ያሳሰቡት ፕሬዚዳንቱ ዩኒቨርሲቲው የግንባታ ስራውን ባጠረ ጊዜ አጠናቆ ለባለቤቶቹ እንደሚያስረክብ ገልጸዋል።

## የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች የችግኝ ተከላ አካሄዱ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ሐምሌ 10 ቀን 2017 ዓ.ም "በመትከል ማንሰራራት" በሚል መሪ ቃል በተጀመረው የ2017 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የችግኝ ተከላ ስነስርአት አካሄዱ ።



ስነስርአቱ የተካሄደው ዩኒቨርሲቲው በአምስት አመት ውስጥ የችግኝ ልማት ለማካሄድ ከለሚኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በተረከበው 3025 ካሬ ሜትር መሬት ላይ ነው። በዚህ የመጀመሪያ ዙር በሆነው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ላይ የዮንቨርስቲው ማህበረሰብ የተሳተፈ ሲሆን፣ የተተከሉት ችግኞች የውበት እና የጥላ መሆናቸው ታውቋል። በመርሃ ግብሩ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል የሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ንጉሥ ታደሰ (ዶ/ር) በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የተተከሉት ችግኞች የማያቋርጥ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ሲገልጹ፣"ችግኝ ማሳደግ ህጻን እንደማሳደግ የማያቋርጥ እንክብካቤ ይጠይቃል።" ብለዋል። አስከትለውም የተረከብነው የችግኝ መትከያ ስፍራ



በከተማ መሀል የተሰጠ መሆኑን አስገንዝበው፣ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ትኩረት በመስጠት መንከባከብ እንደሚገባው አሳስበዋል።



## 18ኛው ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን በኢፐሰዩ ተከበረ

18ኛው ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን በኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጥቅምት 03 ቀን 2018 ዓ.ም ተከበረ:: ‘ሠንደቅ ዓላማችን ለኢትዮጵያ ታላቅ የከፍታ ዘመን ብስራት፤ ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ሕዳሴ’ በሚል መሪ ሀሳብ ሠንደቅ ዓላማ በመስቀል ተከብሯል።







## በኢሲሰዩ የማዕድ ማጋራት መርሀ-ግብር ተከናወነ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የ 2018 ዓ.ም አዲስ ዓመት የዘመን መለወጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ ዝቅተኛ ገቢ ለሚያገኙ ለዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ሰራተኞች የማዕድ ማጋራት መርሀ-ግብር ጳጉሜ 4 ቀን 2017 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ ተካሄደ። በመርሀ-ግበሩም 837 ሰራተኞች ከ 25 እስከ 50 ኪሎ ግራም ዱቄትና የ5 ሊትር የምግብ ዘይት ተለግሷል።



በማዕድ ማጋራቱ ተሳታፊ የሆኑ ሰራተኞችም የዩኒቨርሲቲው አመራር የሰራተኞቹን የኑሮ ሁኔታ በመገንዘብ ላደረጉ ድጋፍ የተሰማቸውን ከፍተኛ ደስታ ገልጸዋል። ሰራተኞቹም አክለው በዩኒቨርሲቲው ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው እና የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞችን ለማገዝ የተደረገው ይህ ድጋፍ ሰራተኞች በዓሉን በፍቅር እና በደስታ እንዲያሳልፉ ከቅንነት እና ፍጹም ሰብዓዊነት የመነጨ አስተሳሰብ መሆኑን ገልጸው ይህን ተነሳሽነት በመውሰዱና ሂደቱን እስከ መጨረሻው በመከታተል ድጋፉ እንዲደረግ ላደረገው ለዩኒቨርሲቲው አመራር ልባዊ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡ ፡ ለመላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና አመራርም መጪው ዘመን የደስታና የፍቅር ብሎም የመተባበርና የዕድገት እንዲሆን ያላቸውን መልካም ምኞት ገልጸዋል።





# ECSU Presedident and GIZ Explore Collaborative Opportunities

Dr. Nigus Tadesse, President of the Ethiopian Service Service University (ECSU), met with a team from the Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) on September 2, 2025 to discuss potential bilateral cooperation. The discussions focused on exploring opportunities to strengthen ECSU's ongoing training and educational initiatives through collaborative efforts.



Dr. Nigus Tadesse extended a warm welcome to the GIZ team, expressing sincere appreciation for their interest in collaborating with ECSU. He provided a comprehensive overview of the university's current status, underscoring its crucial role in the national reform agenda. Dr. Nigus highlighted that ECSU is



currently undergoing a transformative reform aimed at cultivating a highly productive civil service and supporting national efforts to build competent public servants. He also emphasized the university's close working relationship with the Civil Service Commission and detailed various reform initiatives that showcase ECSU's commitment to excellence and national development.

In response, the GIZ team thanked Dr. Nigus for his warm reception and the opportunity to explore a potential partnership. They expressed their keen interest in collaborating with ECSU across three key areas: Fair Administration, Democratic Participation and Civic Education.



Both parties expressed optimism about the potential for a fruitful partnership, envisioning a collaboration that will significantly contribute to strengthening Ethiopia's civil service and advancing the nation's development goals. The meeting concluded with a mutual agreement to explore the outlined areas further and work towards formalizing the cooperation.

# Case Teaching Workshop Held at ECSU

Ethiopian Civil Service University's (ECSU) College of Finance, Management and Development (CFMD) held a significant workshop on case-based teaching in collaboration with the world-renowned Ivey Business School on July 16,2025 .

The event, titled "Teaching with Cases, 39 Country Initiative, Ivey Publishing Case Collection," brought together academic staff and experts from across the university. Dr. Lemma Gudissa, ECSU's Vice President for Academic Affairs, opened the workshop by underscoring the importance of case-based teaching in modernizing education for national impact. He called on the attendees to contribute their on-the-ground expertise to the case discussions, making the learning experience more robust. He gratefully acknowledged the 39 Country Initiative for two key





contributions: providing access to a global collection of impactful case studies and, crucially, building the capacity for ECSU to create its own localized case materials grounded in Ethiopian realities. He concluded with sincere thanks to the organizers for promoting this highly practical and effective learning methodology. The workshop's facilitator, Dr. Yamlaksira Getachew, an Associate Professor of Strategy at Babson College, led detailed discussions on several key topics. These included "Taking Stock of the Lecture-Based Approach," "The Case-Based Approach," "Applying the Case-Based Approach," "The Value of the Case-Based Approach," the "39 Country Initiative," the "Ivey Publishing Case Collection," and "Case-Based Education." Participants actively engaged in the sessions, raising various points and holding extended discussions on the topics presented by Dr. Yamlaksira . Dr. Yamlaksira Getachew holds a Ph.D. in Business Administration from the Ivey Business School at Western University, Canada, and an MBA from Addis Ababa University.He has authored two strategy cases, one on Ethiopian Airlines and another on a Kenyan social enterprise dedicated to tackling poverty.



# Ethiopian Public Service University

Contact Address:
Hot line:+251-116-46-30-15
Tel: 0116462887
Fax: 0116463016
P.O.Box: 5648
E-mail: IPRD@ecsu.edu.et
pr.ecsu@gmail.com
Website: www.ecsu.edu.et
Tweeter:@ECSU tweets
Telegram: htpps://t.me/ecsutelegram
YouTube: htpps://www.youtube.com/Ethiopia
FM Radio: 100.5
Facebook: Ethiopian Public Service University